በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 232284
ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዝማም አስረስ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አያልነሽ ገነት

2. ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ገነት

3. ወ/ሮ ጥላነሽ ገነት

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ክልል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ሜጫ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0150251 ግንቦት 19 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የገጠር መሬት ድርሻ ለመካፈል እና የሰብል ግምት ለማስከፈል የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ሜጫ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ሟች አባታችን አቶ ገነት ደምሴ እና ሟች እናታችን ወ/ሮ ጠጋዬ ይታይህ በ1989 ዓ.ም፣ 1996 ዓ.ም እና 1997 ዓ.ም አከራካሪውን መሬት በስማቸው ይዘው ሲጠቀሙበት ነበር፣ እናታችን በ 2006 ዓ.ም አባታችን ደግሞ በ 2013 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አመልካች እና ልጆች በጋራ በመሆን በአካባቢው ሽማግሌዎች በቀን 03/06/2014 ዓ.ም ሐብት ንብረት ከፍላ ሰጥታናለች፣ በኋላ ተመልሳ ውል አፍርሳለች፣ ስለሆነም አዋሳኛቸው በክሱ ተ.ቁ 1፣ 2 እና 3 ላይ የተገለጹ መሬቶች በመጀመሪያ የእናታችን ድርሻ ከላዩ እንዲነሳ፣ የአባታችንን ድርሻ ደግሞ ከአመልካች ልጆች ጋር ድርሻችን እንዲሰጠን፣ በክሱ ተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው መሬት ላይ ያለ 42 ዚንጎ ግምቱ 60000 የሆነ ድርሻችን እንዲሰጠን፣ በዚሁ መሬት ላይ እና በተ.ቁ 2 እና 3 ላይ ያሉ ባሕር ዛፎች እና ሰብሎች ግምት እና አባታችን የቆጠበው የቁጠባ ገንዘብ ግማሹን በዓይነት እንድትሰጥ ወይም ግምቱን ብር 104000 እንድትከፍል ውሉን ስላፈረሰችም ብር 50000 እንድትከፍል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እናት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ከ1989 ዓ.ም የመሬት ሽግሽግ በፊት ነው፣ ስለሆነም የእናታችን ድርሻ ይሰጠን በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላቸውም፣ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ የሟችን ንብረት ለመጠየቅ ሟች በሞተ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ ይገባል፣ የ 3ኛ ተጠሪ እናት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት የ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እናት ከሞተች በኋላ ነው፣ ሟች አባታቸው ያገባት በ1989 እና 1996/97 መሬት ስላልተመራች የእናቴ ድርሻ ይሰጠኝ ብላ መጠየቅ አትችልም፣ ከሟች ባለቤቴ ጋር መሬት አልተመዘገበችም አልተቆጠረችም፣ *አመልካች እና ሟች አባታቸው በአከራካሪው መሬት በጋራ ተመዝግበንበታል፣* ስለሆነም መሬቱን ሊጠይቁኝ አይችሉም፣ ሰብልም ምርትም ሊካፈሉ አይገባም፣ መሬቱን ከባለቤቴ ጋር የተመዘገብንበት እና የተቆጠርንበት ስለሆነ ድርሻዬ ቅድሚያ እንዲወሰንልኝ፣ የአባታቸው ድርሻ ግን ከእኔ የተወለዱ ስድስት ልጆች ስላሉ እንደልጅ እኩል ቢካፈሉ ተቃውሞ የለኝም፣ በሽማግሌ መደራደሬ አይካድም ነገርግን እናታቸው መብትና ጥቅም የላትም በምልበት ጊዜ ሽማግሌ አስገድዶ ቢያስፈርመኝም ውሉ ለሕግ እና ለሞራል ተቃራኒ ስለሆነ እና እኔን የሚጎዳ እና የልጆቼን ጥቅም የሚያሳጣ ስለሆነ ፈርሷል አልፈረምኩም በማለት በሽማግሌዎች አሳስቤአለሁ፣ ቤቱ 42 ዚንጎ ሳይሆን 29 ዚንጎ ነው፣ የእኔ ድርሻ ተነስቶ እንደልጆች ቢካፈሉ ተቃውሞ የለኝም፣ አምርቼ የተጠቀምኩት የሰብል ግምት የለም፣ አለ እንኳን ቢባል ለቀብር ማስፈጸሚያ እና እስከ 40 ያወጣሁት ወጪ ተቀንሶ ቢካፈሉ ተቃወሞ የለኝም፣ ስለሆነም የተጠሪዎች ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች እና የፍርድ ቤቱን ማጣሪያ ምስክሮች ከሰማ እና ከሚመለከተው የወረዳው መሬት አስተዳደር ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በግራቀኙ ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያሳዩት አከራካሪው መሬት በ1989 ዓ.ም በነበረው የመሬት ድልድል ሟች አቶ ገነት ደምሴ እና የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ወላጅ እናት ጸጋዬ ይታይህ የተመሩት መሆኑን እና በዚህ ወቅት አመልካች ያልነበረች እና ያልተመራችው ከአራት

*ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ዓመት በኋላ በ 1993 ዓ.ም ያገባት እና በክሱ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእጅዋ የሚገኙ መሆኑን ነው፤ ስለሆነም በክሱ ተ.ቁ 1፤ 2 እና 3 የተጠቀሱት መሬቶች ሟች አቶ ገነት ደምሴ በ 1989 ዓ.ም ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ወላጅ እናት ወ/ሮ ጸጋዬ ይታይህ ጋር የተመሩት በመሆኑ የእናታቸውን ድርሻ ለቃ ታስረክባቸው፤ 3ኛ ተጠሪ የሟች ጸጋዬ ይታይህ ልጅ ስላልሆነች ልታገኝ አይገባም፤ ቀሪው መሬት የሟች ገነት ደምሴ መሬት መሆኑ ስለተረጋገጠ እና አመልካች በዚህ መሬት ላይ ውል የሌላት በመሆኑ ለተጠሪዎች እና ለአመልካች ልጆች ሊከፋፈል ይገባል፤ ዳገሳ ከአመልካች ቀለብ ስለማይተርፍ ልታካፍል አይገባም፤ በቆሎ በሟች መሬት ላይ ያመረተችው በመሆኑ ግማሹን ታካፍል፤ 30 ዚንጎ ቤት እንዳላቸው ስለተረጋገጠ ግማሹ ለአመልካች ሆኖ ግማሹ ልጆቹ በዓይነት ወይም ግምቱን ይካፈሉ፤ የበሬ ግምት ግማሽ ብር 15000 ታካፍላቸው፤ የቁጠባ ገንዘብ ግማሽ ብር 10000 ታካፍላቸው፤ ባሕርዛፍ እንዳለ በማስረጃ አልተረጋገጠም፤ የእርቅ ውሉ ግልጽነት የሌለው እና የተቃወመችው በመሆኑ ውል ላፈረሰ ልትከፍል አይገባም  በማለት ወስኗል። ይህም ውሳኔ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጸንቷል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም  ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ያለበቂ ምክንያት አልፎብኛል፤  ሟች ባለቤቴ እኔን ከማግባቱ በፊት ወ/ሮ ንግስቴ አወቀ የተባለችውን አግብቶ በተፈጠረው አለመግባባት ከተለያዩ በኋላ ሰኔ 7 ቀን 1993 ዓ.ም ከእኔ ጋር ጋብቻ ፈጽሟል፤ ከአንድ ዓመት ወዲህ በፍቅር ጠብ ቢመጣ ሰብል ልትካፈል ከ2 ዓመት በኋላ ከወለደች ከከበደች በሟች ባለቤቴ ስም የተመዘገበው መሬት እኩል ልንካፈል ተስማምተናል፤ በ1996/97 የመሬት ቆጠራ ምዝገባ አስመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር AE/77/23/292 ደብተር በስማችን ይዘንበታል፤ የአመልካች ምስክር ይዞታው በጋራ ተመዝግቦ ፎቶ ተለጥፎ ማየቱን መስክሯል፤ የተጠሪዎች እናት ከ 1989 ዓ.ም የመሬት ሽግሽግ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለየች  እና ባችማ በሚባል ቀበሌ እንደተቀበረች ተረጋግጧል፤ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤቱ የተመሰረተው እና መረጃ መመዝገብ የጀመረው ከ 1995 ዓ.ም ጀምሮ ነው፤ ከዚህ በፊት የተለያየ መረጃ ከመሰጠቱ አኳያ ጉዳዩ በሕዝብ ተሳትፎ እና በገልለተኛ አካል አልተጣራም፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የእርሻ መሬት ላይ የአሁን አመልካች ከሟች ባለቤቷ አቶ ገነት ደምሴ ጋር በ1994 ዓ.ም ጋብቻ መስርታ ለ20 ዓመታት የተጠቀመችበትን የእርሻ መሬት በተመለከተ ሟች አቶ ገነት ደምሴ እና የተጠሪዎች እናት ሟች ጸጋዬ ይታይህ በ 1989 ዓ.ም የተደለደሉት በመሆኑ የአሁን አመልካች አከራካሪው የእርሻ መሬት ምንም አይገባትም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መጋቢት 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የተጠሪዎች ወላጆች አከራከሪው መሬት እንደተደለደሉ ተረጋግል፤ አመልካች በ 1996 ዓ.ም የመሬት ቆጠራ ወቅት ራስዋ

የተደለደለችው ሌላ 3 ቃዳ መሬት አላት፤ አመልካች መሬት ለመካፈል የተስማማች መሆኑን የሚያስረዳ የጋብቻ ውል ሰነድ የለም፤ አመልካች ሰብል በስምምነት መጠቀምዋ የጋራ መሬት እንዳላት አያመለክትም፤ ምስክሮችዋም አላስረዱም፤ አመልካች በሚቆች ወላጆቻችን መሬት ላይ ስምዋ አልተመዘገበም፤ ባለይዞታ እና ባለመብት ባለመሆንዋ ከአዋጁ አንቀጽ 55/1 አንጻር የይርጋ መቃወሚያ ማንሳት አትችልም፤ እናታችን ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችው በ 2006 ዓ.ም ነው፤ ስለሆነም ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

3ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካችም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች የሚመሩት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ነው፡፡ ግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች  ክርክራቸው ለማስረዳት ያስችሉናል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222፤ 223 እና 234 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በቃል ተሰምቶና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247፣ 248 እና 249 ድንጋጌዎች አግባብ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ ለጉዳዩ በሕጉ አግባብ የቀረቡት የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች ተሰምተውና አስፈላጊ ሲሆንም በሕጉ አግባብ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ በማድረግ ጉዳዩን በሚገባ አጣርቶ ፍትሐዊ ዳኝነት መስጠት ያለበት መሆኑን በዚሁ ሕግ ቁጥር 257፣ 258 እና 259 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም ፍርድ ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ እውነቱን አጣርተው ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች የተጠሪዎች አባት ከሆኑት ከሟች ባለቤቷ ጋር በመሆን አከራከሪው መሬት በስማቸው የተመዘገበ መሆኑን በመግለጽ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበችው ክርክር በተጠሪዎች አልተካደም፡፡  የስር ፍርድ ቤት አከራካሪውን መሬት በ1989 ዓ.ም በነበረው የመሬት ድልድል ሟች አቶ ገነት ደምሴ እና የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ወላጅ እናት ጸጋዬ ይታይህ የተመሩት በመሆኑ የእናታቸውን ድርሻ ለቃ ልታስረክባቸው ይገባል በማለት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በቀር አመልካች አከራከሪው መሬት ላይ ከሟች ባለቤታቸው ጋር በመሆን በይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ተመዝግበንበታል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ በውሳኔው ላይ ምንም ያሰፈረው ነገር የለም፡፡

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 2 የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የባለይዞታው በሕግ የተጠበቀ ማስረጃ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 35(4) የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንደኛው ስም ብቻ ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኂላ ጋብቻ የተፈጸመ እንደሆነ ተጋቢዎች መሬቱን የጋራ ይዞታ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ፤ ባልና ሚስት የግል የነበረውን መሬት በስምምነት የጋራ በሚያደርጉበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በሁለቱ ስም ይዘጋጃል በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክርክር ከሟች ባለቤታቸው ጋር ከተጋቡ በኂላ አከራካሪው መሬት በሁለቱም ስም በይዞታ ማረጋጫ ማስረጃ ላይ የተመዘገ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ይህ ክርክራቸውም በተጠሪዎች አልተካደም፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ እስከተከራከሩ ድረስ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በእርግጥም አመልካች እንደሚሉት አከራከሪው መሬት በአመልካች እና በሟች ባለቤታቸው በጋራ የተመዘገበ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት አጣርቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤቱ ይህን ሳያደርግ አከራካሪውን መሬት በ1989 ዓ.ም በነበረው የመሬት ድልድል ሟች አቶ ገነት ደምሴ እና የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ወላጅ እናት ጸጋዬ ይታይህ የተመሩት በመሆኑ የእናታቸውን ድርሻ ለቃ ልታስረክባቸው ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ክልል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰ/ሜጫ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0150251 ግንቦት 19 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የባሕርዳር እና አከባባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 31738 ሠኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 115259 ሠኔ 16 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በክሱ ተ.ቁ 1፤ 2 እና 3 የተጠቀሱት መሬቶች ሟች አቶ ገነት ደምሴ በ 1989 ዓ.ም ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ወላጅ እናት ወ/ሮ ጸጋዬ ይታይህ ጋር የተመሩት በመሆኑ የእናታቸውን ድርሻ ለቃ ልታስረክባቸው ይገባል በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ቀሪው የውሳኔ ክፍል በዚህ ውሳኔ አልተነካም፡፡
3. የሰ/ሜጫ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በክሱ ተ.ቁ 1፤ 2 እና 3 የተገለጹትን መሬቶች በሚመለከት ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

*ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም